# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 235 ህዳር 6 2005 ገጽ 1


የትግራይ ህዝብ እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ ስለ አንድነት፣ ስለዲሞክራሲ፣ ስለሰበአዊ መብትና መልካም አስተዳደር ጠንቅቆ የሚያውቅና ለነዚህ መሰረታዊ ጥያቄዎች እስከ ህይዎት መሰዋእትነት የሚታገል ህዝብ ነው እንጅ፤ እነ አዜብ እንደሚያዎሩት ዳቦ እንወረውርልሃለን ዝም በል የሚባል ህዝብ እንዳልሆነ ሊረዱት እና ሊያጤኑት ይገባል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ደራ ወረዳ ዉስጥ የፈጸመዉ ኢሰብዓዊ ድርጊት ከፍተኛ ህዝባዊ ቁጣ ቀሰቀሰ

የወያኔ ሹመኞች በአማራ ክልል ደራ ወረዳ ውስጥ የፈጸሙት አስጸያፊ ተግባር እነዚህ ዘረኞች በኢትዮያና በህዝቦቿ ላይ ምንም አይነት ዉርደት ከመፈጸም ወደኋላ እንደማይሉ በግልጽ የሚያሰይ ነዉ ሲሉ አንድ ድርጊቱን የተመለከቱ የአገር ሽማግሌ ተናገሩ። ኢኚሁ ስማቸዉ እንዳየጠቀስ የፈለጉ የአገር ሽማግሌ ጨምረዉ እንደገለጹት የአንድ አገር ዜጋ በተለይ ህዝብን እመራለሁ የሚል አካል በህዝብ ላይ እንዲህ አይነት በደል ሲፈጽም በታሪካችን ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም ብለዋል።

በአማራ ክልል የግብርና ልማት ቢሮ ውስጥ በማገልገል ላይ የሚገኙ አንድ ባለሙያ እንደተናገሩት፣ የወያኔ አገዛዝ ደረጃ በደረጃ ህዝብን በፍርሃትና በጉልበት በማሸማቀቅ፣ በህይወት ታሪካችን ሰምተንና አይተን የማናውቀውን ግፍና ተግባር እየፈጸሙብን ነው ብለዋል። በማያያዝም የወያኔን ድርጊት የአማራ ክልል ህዝብ በንቃት እየተከታተለዉ መሆኑን ተናግረዉ ህዝብ ከአሁን በኋላ የሚጠብቀዉ አመቺ ሁኔታ እስኪፈጠር ብቻ ነዉ ብለዋል። ባለሙያዉ በመጨረሻ በሰጡት አስተያየት ሊነጋ ሲል ይጨልማል እንደሚባለው፣ ወያኔ እየፈጸመ ያለው ግፍና በደል ለስርዓቱ ውድቀት መቅረብ አመላካች ስለሆነ ሁላችንም ከዚህ ግፍና በደል ነጽ ለመውጣን በአንድነት መነሳት አለብን ብለዋል።

በተመሳሳይ መልኩ በደቡብ ወሎ ዞን ወልዲያ ከተማ በንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ ግለሰብ በስልክ በሰጡን አስተያየት እንደተናገሩት፣ ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ እንዲህ አይነቱን በደል የሚፈጽመው በፍጹም ሊባል በሚችል መልኩ ከኢትዮጵያዊያን ልብ "አክ እንትፍ" (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ኢትዮጵያ ውስጥ ሙስና እጅግ አስከፊና አሳሳቢ ደረጃ ላይ እንደደረሰ ተገለጸ

ኢትዮጵያ ውስጥ በአገዛዙ ስር ባሉ ተቋማት ውስጥ የገንዘብ ዝርፊያ እየተባባሰና ከቁጥጥር ውጪ እየሆነ መምጣቱን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ በላከልን ዘገባ አመለከተ። በአዲስ አበባ መንገዶች ፕሮጀክት ግንባታ ዙሪያ እየተፈጸመ ያለውን ምዝበራ ዋቢ በማድረግ ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ በላከልን ዘገባ መንገዶች ይሰራሉ ህንፃዎች ይገነባሉ እየተባለ በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ወጪ ከሆነባቸው በኋላ የመንገዶቹና የህንጻዎቹ ጥራት ወጣ ከተባለዉ ወጪ ጋር በፍጹም እንደማይገናኝ ለማወቅ ተችሏል።

ከዚሁ ዝርፊያና ምዝበራ ጋር በተያያዘ የአገዛዙ ባለስልጣናትና ህንጻ ተቋራጮች በየጊዜው እንደሚሰበሰቡና ስብሰባዎቹ በኃይለ ቃል ተጀምረው በስድብ እንደሚጠናቀቁ ለማወቅ ተችሏል። በተለይም ግንባታዎቹን ለማከናወን ውል በወሰዱ የግንባታ ስራ ተቋማትና ስራው እንዲከናወን በጠየቁ የአገዛዙ ተቋማት መካከል ከፍተኛ የሆነ ፍትጊያና መጎነታተል እንዳለ የታወቀ ሲሆን ለዚህም ፍትጊያ ዋናዉ መንሴው ለግንባታ ስራ የሚመደብ ገንዘብ በሙስና በበርካታ ግልሰቦች ኪስ እየገባ በመሆኑ ነው ተብሏል።

## መንግስታዊ ያልሆነው የጀርመን ድርጂት ቢሮውን ዘግቶ ከኢትዮጵያ ወጣ

በአቶ ፓትሪክ በርግ ሲመራ የነበረውና ኢትዮጵያ ውስጥ ሰፊ የሥራ ስምሪት የነበረው ጀርመናዊው መንግስታዊ ያልሆነው የሄነሪ ቦር ፋውንዴሽን ቢሮውን ዘግቶ ወደ ሀገሩ መመለሱ ታወቀ። ይህ በዲሞክራሲ መስፋፋትና በሰብዓዊ መብቶች መከበር ላይ የሚያተኩረዉ ፋውንዴሽን ጨርቁን ጠቅልሎ ከኢትዮጵያ የወጣዉ ኢትዮጵያ ዉስጥ የሚታየዉ የመብት ረገጣና የህዝብ ድምፅ መታፈን የወያኔ ስርአት በስልጣን ላይ እስካለ ድረስ አይወገድም የሚል ግንዛቤ ላይ በመድረሱ ነዉ። ከፋውንዴሽኑ ከአገር መልቀቅ ጋር በተያያዘ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ለዝግጅት ክፍላችን እንደተናገሩት እንዲህ አይነት ፋውንዴሽኖች ኢትዮጵያን እየለቀቁ መውጣታቸው የሰብአዊ መብት አከባበር ኢትዮጵያ ዉስጥ ወረቀት ላይ ከመስፈር የዘለለ ሌላ ምንም የሚሉት ነገር እንደሌለ ተናግረዋል።

የፋዉንዴሺኑ የኢትዮጵያ ዘርፍ ሊ/መንበር ወ/ሮ ባርበራ ኡንቢግ ኢትዮጵያን ለቅቀዉ ሲወጡ እንደተናገሩት በዲሞክራሲ፤ (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

## ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ከአሁን በኋላ በንብረት ጉዳይ ፍርድ ቤት አታቅርቡኝ አለ

"እኔም ሆንኩ ባለቤቴ በንብረት ውርስ ምክንያት መከራከር አንፈልግም:: በዚህም ምክንያት ወደ ፍርድ ቤት ከዛሬ በኋላ እንዳልቀርብ ለማረሚያ ቤት ትዕዛዝ ይሰጥልኝ፤" ሲል ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ፍርድ ቤቱን መጠየቁን የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት ዘገበ።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ በግፈኛው የወያኔ አገዛዝ አቃቤ ህግ ንብረታቸው እንዲወረስ የተጠየቀባቸው ፍርደኞች ዉስጥ በዕድሜ ልክ ፅኑ እሥራት እንዲቀጣ የተወሰነበት አንዱዓለም አራጌ በ15 ዓመታት ፅኑ እሥራት እንዲቀጣ የተወሰነበትና በአሜሪካ የሚኖረው ጋዜጠኛ አበበ በለው ይገኙበታል። ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ በገገር ውስጥ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን በፍርሃትና በመሸማቀቅ ጸጥ ብለው እንዲገዙ ከዚህ ጋር በተያያዘ ቀደም ብሎ ጋዜጠኛ አበበ ገላው የወያኔ ድርጊት ኢትዮጵያ ውስጥ ንብረት ያላችሁ በውጪ የምትኖሩ ሰዎች አርፋችሁ ካልተቀመጣችሁና መንግስትን ከተቃወማችሁ ንብረታችሁ ይወረሳል ለማለት እንደሆነ ማመልከቱን ኢሳት ገልጾ ጋዜጠኛ አበበ፤ ቤቱ የሱ አይደለም እንጂ ቢሆን እንኳ ለፍትህና ለነፃነት ስለታገለ ብቻ ንብረቱ መወረስ እንደሌለበት ተናግሯል።

እንደ ኢሳት ዘገባ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ከተቀመጠበት የተከሳሾች መቀመጫ ሳጥን ውስጥ ቆሞ የሚያቀርበው ሐሳብ እንዳለው ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት በማግኘቱ ጥያቄውን በአጭሩ ያቀረበ ሲሆን "እኔም ሆንኩ ባለቤቴ በንብረት ውርስ ምክንያት መከራከር አንፈልግም:: በዚህም ምክንያት ወደ ፍርድ ቤት ከዛሬ በኋላ እንዳልቀርብ ለማረሚያ ቤት ትዕዛዝ ይሰጥልኝ፤" በማለት መናገሩ ታውቋል:: እስክንድር ነጋ የአሸባሪነት ክስ ተመስርቶበት የ18 አመት እስራት የተፈረደበት ሲሆን ይህ ጀግና ጋዜጠኛ በወያኔ ዘመን እየታሰረ ወህኒ ሲወርድ የአሁኑ ለዘጠነኛ ግዜ መሆኑ ታዉቋል። ባለፈዉ ሳምንት መጨረሻ ላይ ፍርድ ቤት ቀርቦ የነበረዉ እስክንድር ነጋ ሊጠይቀው የሄደውን የ6 አመት ልጁን ናፍቆት እስክንድርን ስራዕቱ ሲለወጥ ቤትህን ታግኝዋለህ በማለት አይቀሬዉን የወያኔ ስርአት መወገድ ፍርድ ቤት ዉሰጥ ፖሊሶች እየሰሙ ተናግሯል።

## በሶማሌ ክልል የሚታየዉ የመብት ረገጣ እየተባባሰ መሄዱ ተሰማ

ከኢትዮጵያ ፌዴራል ክልሎች አንዷ በሆነችዉ ሶማሌ ክልል ዉስጥ በተለያየ መልኩ በዜጎች ላይ የሚደርሰዉ የመብት ረገጣ ከግዜ ወደ ግዜ እየባሰበት መጥቶ በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረሱን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ አመለከተ። በጅጅጋ አካባቢ የሚገኘው ዘጋቢያችን ያናገራቸው የከተማዋ ነዋሪዎችና ሰራተኞች እንደገለጹት የሶማሌ ክልክ ርዕሰ መስተዳድር ዋና ከተማ በሆነችው ጅጅጋና በአካባቢዋ ከፍተኛ የሆኑ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች በአካባቢዉ ተወላጆችና በክልሉ ውስጥ በሚኖሩ የሌሎች አካባቢዎች ተወላጆች ላይ እየተፈጸመ ነው።

በተለይ ከሌሎች የአገሪቱ አካባቢዎች የመጡ ኢትዮጵያዉያን ሶማሊኛ ቋንቋ አትናገሩም በሚል ሰበብ ከስራ በመባረር ላይ መሆናቸዉም የደረሰን ዘገባ ያመለከተ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ከክልሉ ዉጭ የመጡ ዜጎችን አበሳጭቶ ከክልሉ እንዲሄዱ ለማድረግ በሚደረገዉ ጥረት አነስተኛ ገቢ ያለቸዉንና በቀበሌ ቤቶች የሚኖሩ ዜጎችን በየወሩ ከ500 እሰከ 1500 ብር እንዲከፍሉ የማድረግ ዘመቻ መጀመሩ ታውቋል።

በተያያዘ ዘገባ በቅርቡ ከስልጣን የተባረረዉ የክልሉ ፕሬዚዳንት የመለስ ዜናዊን ሞት ተከትሎ ከእንግዲህ ከማንም ትእዛዝ አልቀበልም በማለት ክልሉን ራስ ገዝ አደርጋለሁ እያለ የክልሉን ሰላምና ጸጥታ የባሰ ችግር ዉስጥ መክተቱም ታውቋል።

## ሚዛን ተፈሪንና አካባቢዋን ከአንድ ወር በላይ ያናወጠዉ ግጭት አሁንም እንደቀጠለ ነዉ

በደቡብ ብሔር ብሐረሰቦች ክልል ከሚዛን ተፈሪ ከተማ 90 ኪሎ ሜትር ወጣ ብሎ በሚገኘዉና ልዩ ስሙ ዲማ ተብሎ በሚጠራው ቦታ በሱርማና በዲዞ ብሔረሰቦች መካከል ከአንድ ወር በፊት የተቀሰቀሰዉ የጎሳ ግጭት የሚያበርደዉ ጠፍቶ በርካታ የአካባቢው ነዋሪዎችን እየጎዳ መሆኑ ተሰማ። በደቡብ ምዕራብ የአገራችን ክፍል በኢትዮጵያና በደቡብ ሱዳን ድንበር አካባቢ የሚኖሩት የሱርማ ብሄረሰብ አባላት ህገ-መንግስቱ ያጎናጸፈን የፖለቲካና የሲቪል መብቶች አልተከበሩልንም የሚል ተደጋጋሚ ጥያቄ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት አቅርበዉ ምክር ቤቱ ጥያቄያቸዉን እንዳልተቀበለዉ የሚታወስ ነዉ። ይህ በእንዲህ እንዳለ እነዚሁ የሱርማ ብሔረሰብ አባላት ለዘመናት የኖሩበትን (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የትግራይ ህዝብን ማታለል ይብቃ! በቃ!

በትግራዩ ህዝባችን ስም የሚደረገው ንግድ አሁንም ከ21 የግፍና የከፋፍለህ ግዛ አመታት በኋላ ተባብሶ እንደቀጠለ ነው። ዘረኛው የወያኔ ቡድን ህወአት "እውነት እውነት እላችኋለሁ መለስ ከመሞቱ በፊት ለትግራይ ህዝብ ያስቀመጠው ጣፋጭ ከረሚላ አለ እና ዝም በሉ" ሲሉ ይደመጣሉ። የትግራይ ህዝብ እንደ ሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ የስርአቱ የስቃይ፣ የሰቆቃ፣ የስደት፣ የግድያና የእስራት ገፈት ቀማሽ ነው። ከጥቂት የሕወአት ጎጅሌዎች በስተቀር! ታዲያ ይህንን እውነት በጠራራ ጸሃይ ላይ በህወአት/ወያኔ የጨለማ ዘመን የሚኖረውን ምስኪኑን የትግራይ ህዝብ ለመካድ እና እንደ ህጻን ልጅ የሚጣፍጥ ከረሚላ አዘጋጅተንልሃል እና ስለዲሞክራሲ ስለነጻነት አትናገር አትጠይቅ ዝም በል አታልቅስ በሚል የማታለል ስራቸውን አሁንም በማደስና ተግባራዊ ለማድረግ በአምባገነኑ የሚቹ ባለቤት አዜብ መስፍን አማካኝነት የትግራይ ህዝብን ለመስበክ ያስባሉ።

የትግራይ ህዝብ እንደሌሎቹ የሀገሪቱ ህዝቦች በችግር የሚገኝ ህዝብ እንጅ እንደ ህወአት ባለስልጣኖች ደልቶት የሚኖር ህዝብ አይደለም። ይሁን እንጅ ወያኔ የትግራዩን ህዝባችንን ከተቀረው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ለማጋጨት ብዙ ሙከራዎችን ላለፉት 21 አመታት ሲያደርጉ ቆይተዋል። መለስ ትግራይን የኢንደስትሪ ማእከል ለማድረግ ያዘጋጀው ፕላን እጇ ላይ ይገኛል የሚሉት አዜብ *"ለህዝብ የሚጠቅም ፕላን ከነበረ ምነው በሚስጥር መለስ እስኪሞት ተጠበቀ?"* ቢባሉ የሚሉት ምንም ነገር አይኖራቸውም፤ ይልቁንም ይህ የሚያሳየው በአሁኑ ሰአት በትግራይና አካባቢዋ በየግዜው የሚነሳውን ተቃውሞና በአካባቢው ብረት አንስተው እንታገላችኋለን የሚሉትን የትግራይ ተወላጆችን የነጻነት ጩኸት ላንቃን ለመዝጋት የታሰበ ነው። ለዚህም ኤፈርት በሚሊዮን የሚቆጠር ሰራተኞችን ቀጥሮ ማስራት እየቻለ ጥቂት የህወአት ጋሻ ጃግሬዎችን ብቻ በማሰራት ትርፍ በማካበት ነገርግን ይህን የሚመለከተውን ሰፊውን የትግራይ ህዝብ ሜዳ ላይ በመጣል የቅርጫው ተካፋይና ተጠቃሚ በማስመሰል ስለ ኢንደስትሪ ማእከል ይለፋፋልናል፡;

የአዜብ መስፍንና የህወአት ወያኔ ጉጅሌዎች በአካባቢው የሚነሳ ጩኸት እንዳይኖርና ጩኸቱ እና እምቢታው እንዳይበላቸው እንዲሁም የበላይነታቸውን አስጠብቀው ለመሄድ የሚያደርጉት መፍጨርጨር ከግዜው እውነታ ጋር ያልተገናዘበ ነው። ዛሬ ትውልድ እንደ ጥዋት ጸሃይ በአዲስ ምእራፍ የአሮጌ አስተሳሰብ ስርአቶችን እየጣለ በአንድነት፣ በመከባበር እና እምቢ አልገዛም በሚልበት ጉዞ ላይ ህወአት/ወያኔ አሁንም በትግራይና በትግራያን መካከልና በተቀረው የኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የከፋፍለህ ግዛ ያረጀ ያፈጀ ፓሊስ እከተላለሁ ብሎ ማሰቡ ሞኝነት ነው። በዚህ የትግራይ ህዝብን ማታለል ከቶ አይቻልም ምክንያቱም የትግራይ ህዝብ በኤፈርት ማን ተጠቃሚ እንደሆነ ነጋሪ ወይም አስረጅ ጎሻሚ አያስፈልገውም።

በኢትዮጵያ የሚደረጉ ማናቸውም የልማት እንቅስቃሴዎች የህዝብን ተጠቃሚነት ማእከል ያደረገ መሆን እየተገባው፤ ህወአት/ወያኔ ግን ለቱባ ባለስልጣናቶቹ እና ለስርአቱ አደርባዮች ብቻ ጥቅምን በማመቻቸትና በመዝረፍ፤ በእጥፍ የኢኮኖሚ እድገት በትግራይ እያገኘን ነው ማለታቸው የተለመደ ቅጥፈታቸው ነው። በአንጻሩ የተቀረው የትግራይ ህዝብ በሀገሩ እንደ ባእዳ እየታዩ የወያኔ ሃብታሞች በደጁ ውስኪ እየተራጩ ሲያልፉ እያዩ ይህ ህዝብ ከቶ እንዴት ሊያታልሉት የሚችል የመስላቸዋል? ይህን ታሪክና ትውልድ የሚፋረጀው ሆኖ እያለ የአንድን ብሄረሰብ ተጠቃሚ በማስመሰል በትግራይ የሚነሳባቸውን የውስጥ ተቃውሞ ለማፈን የታለመ ነው።

የትግራይ ህዝብ እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ ስለ አንድነት፣ ስለዲሞክራሲ፣ ስለሰበአዊ መብትና መልካም አስተዳደር ጠንቅቆ የሚያውቅና ለነዚህ መሰረታዊ ጥያቄዎች እስከ ህይዎት መሰዋእትነት የሚታገል ህዝብ ነው እንጅ፤ እነ አዜብ እንደሚያዎሩት ዳቦ እንወረውርልሃለን ዝም በል የሚባል ህዝብ እንዳልሆነ ሊረዱት እና ሊያጤኑት ይገባል። በተመሳሳይ ህዝቡም በአንድ ድምጽ በስማችን የሚነገደው ንግድ በአስቸኳይ ይቁም በማለት የአምባገነኖችን የከፋፍሎ መግዛት ባህሪ ያለፈበት ያረጀ አስተሳሰብ ከመለስ ጋር የተቀበረ ሃሳብ ነው በሚል እስከመጨረሻው ለአንድነቱ ሊታገል ይገባል።

ልማት በአንድ ክልል ብሄረሰብ ብቻ ከሆነ ጤናማ ያልሆነና አንድነትን የሚለያይ መሆኑን ጠንቅቆ መረዳት ለህወአት ጉጅሌዎች ያስፈልጋቸዋል።

ሁሉም የኢትዮጵያ ህዝብ ትግራይን ጨምሮ በህወአት/ወያኔ አማካኝነት በአንድነታችን የተደቀነብንን የጥላቻና የመከፋፈል አጥር በማፍረስ የኢትዮጵያዊነታችን አንድነት መገለጫችን የሆነውን አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ባንዲራን በማውለብለብ የ21 አመት የከፋፍለህ ግዛ ስርአቱን በአንድ ላይ ልንቀብረው ይገባል!

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ደራ ወረዳ ዉስጥ የፈጸመዉ ኢሰብዓዊ ድርጊት . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ተብሎ መውጣቱን በማወቁና ለጥቂት ጊዜም ቢሆን ስልጣን ላይ ለመቆየት የሚችለው እንዲህ አይነት የጭካኔ ተግባር ሲፈጸም ብቻ ነው ብለዋል። አያይዘውም እንዲህ አይነት የቀብፀ ተስፋ ድርጊት ሁኔታዎችን ከማባባስና የወያኔን ግብአተ መሬት ከማፋጠን ውጭ ምንም መፍትሄን አያመጣምና ከዚህ ግፈኛ አገዛዝ ለመላቀቅ በአንድነት እንነሳ ብለዋል።

ከዚሁ ዘገባ ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት በደራ ወረዳ የተፈጸመው ኢ-ሰብአዊ ድርጊት በሃገር ውስጥ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንን ቁጣ መቀስቀሱን ዘግቧል። ኢሳት ሃገር ውስጥ ከሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ጋር ያደረገውን ቃለምልልስ ዋቢ በማድረግ እንደዘገበው የወያኔው ዘረኛ አገዛዝ ኢትዮጵያዊያን ላይ እየፈጸመ ያለው ዘግናኝ ተግባርና ድርጊት ባስቸኳይ እንዲቆም ሁሉም ኢትዮጵያዊ መነሳት እንዳለበት ያስጠነቅቃል።

የግንቦት ሰባት ሬዲዮ ዝግጂት ክፍል ባለፈው ሃሙስ ዝግጂቱ በውጪ ሃገር ከሚገኙና በደራ ወረዳ በተፈጸመው አጸያፊ ተግባር ቁጣቸውን ከገለጹት ኢትዮጵያዊያን ውስጥ ጥቂቶቹን ማቅረቡ ይታወሳል።

## መንግስታዊ ያልሆነው የጀርመን ድርጂት ቢሮውን ዘግቶ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በሰብዓዊ መብቶችና በጾታ እኩልነት ላይ የሚያረኩረዉ ድርጅታቸዉ መንግስት በሚያደርግበት ጫና የተነሳ ስራዉን ሊሰራ አልቻለም ብለዋል። በቶለይ እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር በ2009 ዓም የወጣዉ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ህግ መንግስት ሆን ብሎ ስራችንን እንዳንሰራ ያወጣዉ ህግ ስለሆን ይህንን ህግ ተከትለን መስራት ስለማንችል ኢትዮጵያን ለቅቀን ለመዉጣት ተገድደናል ብለዋል። ከዚህ በተጨማሪ በየቀኑ የምናየዉና የምንሰማዉ የዜጎች መብት መረገጥ በተለይም የጋዜጠኞችና የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች አላግባብ መታሰር እኛ ከምንሰራዉ ስራ ጋር በቀጥታ የተያያዘ ቢሆንም በአዲሱ ህግ መሠረት እነዚህን ጉዳዮች መከታተል ስለማንችል ያለን አማረጭ የተሻለና ለህዝብ የሚያስብ መንግስት ወዳለበት አገር መሄድ ነዉ ብለዋል።

## ሚዛን ተፈሪንና አካባቢዋን ከአንድ ወር በላይ ያናወጠዉ ግጭት . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

መሬት ለቅቀዉ በደ ሌላ ቦታ እንዲሄዱ በመገደዳቸዉ ቀድሞዉንም በቋፍ የነበረዉ የአካባቢዉ አካባቢዉ ጸጥታ ከቁጥጥር ዉጭ ሊሆን ችሏል።

ብዛት ያለዉ የወያኔ የጸጥታ ሀይል የአካባቢዉን ጸጥታ እንዲቆጣጠርና በሁለቱ ብሔረሰቦች መካከል የተፈጠረዉን ግጭት እንዲያበርድ ወደ አካባቢዉ የተላከ ቢሆንም የወያኔ ሀይሎች ሀይል ከመጠቀም ዉጭ ለእንደዚህ አይነቱ ከፍተኛ ጥንቃቄ ለሚፈልግ ተልዕኮ የተዘጋጁ ባለመሆናቸዉ የጸጥታ ሀይሉ አካባቢዉን ከረገጠበት ግዜ ጀምሮ የለመደዉን ሀይል በመጠቀም ዜጎችን ማሰርና ማሰቃየት በመጀመሩ የአካባቢዉ ጸጥታ ጉዳይ ከድጡ ወደ ማጡ መዉረዱን አንድ ስማቸዉ እንዳይገለጽ የጠየቁን የአካባቢዉ ባለስልጣን ተናግረዋል። በዚህ ሁለተኛ ወሩን በቆጠረዉና ዛሬም ድረስ እልባት ባላገኘዉ ግጭት ዘጠኝ የአካባቢዉ ነዋሪዎች መሞታቸዉንና ቁጥሩ በዉል የማይታወቅ ሰዉ መቁሰሉን ከክልሉ የደረሰን ዜና ያስረዳል።

ሚዛን ተፈሪና አካባቢዉ በተለይ ዲማ ወረዳ በወርቅ ማዕድን የበለፀገች በመሆኗ በሺዎች የሚቆጠሩ የወያኔ አገዛዝ የስራ እድል ሊፈጥርላቸዉ ያልቻለ ኢትዮጵያዉያን ወርቅ አምርተዉ ለመሸጥ ከተለያዩ ክልሎች እየፈለሱ የሚመጡ ሲሆን እነዚህ ስራ ፍለጋ የሚሄዱት ወገኖች በሁለቱ ብሄረሰቦች መካከል የተቀሰቀሰው ግጭት ሰለባ መሆናቸዉ ታዉቋል። በአሁኑ ወቅት ሚዛን ተፈሪና ዲማ ዉስጥ ከፍተኛ ቀዉስና አለመረጋጋት የሚታይ ሲሆን ከቅርብ ግዜ ወዲህ ሚዛን ተፈሪና አካባቢዉ ከተቀረዉ የአገሪቱ ክፍል ጋር በየብስ፤ በአየርና በስልክ የሚያደርጉት ግንኙነት ሙሉ ለሙሉ መቋረጡን በክልሉ የሚገኙ ምንጮቻችን የላኩልን ዜና ያስረዳል።

## "መገንጠል ለሚፈልግ ግዜዉ ሲደርስ መገንጠል መብቱ ነዉ" - በረከት ስምኦን

ኢትዮጵያን ነገስታት መርተዋታል፤ ወታደራዊ አምባገነኖች ጨፍረዉባታል፤ ዛሬ ደግሞ ዘረኛ አምባገነኖች ቁም ስቅሏን እያሳዩዋት ነዉ። እቺን ለአስተዋይ መሪዎች ያልታደለች የአስተዋዮች አገር ዛሬ አለም የሚያዉቃት በድህነት፤ በረሀብና በስደት ነዉ። ድህነት፤ ረሀብና ኋላ ቀርነት ኢትዮጵያ ላይ የተደቀኑ ታላላቅ አደጋዎች ቢሆኑም ዛሬ አገራችን ኢትዮጵያን ከምንም ነገር በላይ የሚያስፈራት ድህነትና ረሀብ ሳይሆን ወያኔ በግድ የጫነባት የመገነጣጠል አደጋ ነዉ።

በአባቶቻችን የደም መስዋዕትነት ተከብሮ የኖረዉ የኢትዮጵያ አንድነት የሚያሳስባቸዉ ኢትዮጵያዉያን "መገንጠል" የሚሉትን አደጋ ሲሰሙ ልባቸዉ የሚቀልጠዉ ወያኔ ህግ በመንግስቱ ዉስጥ መገንጠል ይቻላል ብሎ ስለጻፈ ብቻ አይደለም። አያሌ ኢትዮጳያዉያንን የሚያሳስባቸዉና የሚያስፈራቸዉ ኢትዮጵያ ዉስጥ ቁልፍ ቁልፉን የስልጣን ቦታዎች ቆንጥጠዉ የያዙት ሰዎች የሚናፍቃቸዉ የኢትዮጵያ አንድነት ሳይሆን የኢትዮጵያ መበታተን በመሆኑ ነዉ። ከእነዚህ የኢትዮጵያን ዉድቀትና መበታተን ከሚመኙ ከሀዲ ሰዎች ዉስጥ አንዱና ዋነኛዉ በረከት ስምኦን ነዉ።

በረከት ስምኦን የኢትዮጵያን ትልቅነት የሚያቀልሉና የኢትዮጵያን ህዝብ ማንነት የሚያሳንሱ አያሌ አጥንት የሚሰብሩ ንግግሮች ያደረገ እብሪተኛ ሰዉ ነዉ። በረከት እዉነትን ከዉሸት፤ ቁምነገርን ከቧልት አገርን ያክል ትልቅ ነገርና የቤቱን ጓዳ ለይቶ ማየት የማይችል እንኳን ለአገር ስልጣን ለዕቁብ ዳኝነትም የማይመኙት ሰዉ ነዉ። ሆኖም እሱና የደደቢት ጓደኞቹ አዲስ አበባን ሲቆጣጠሩ የስልጣን መያዣ መለኪያዉ ብስለትና አስተዋይነት ሳይሆን ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን መጥላትና ማጥላላት በመሆኑ በረከት ስምኦን ዛሬም ድረስ እንደጨበጠ የያዘዉን ስልጣን ለመያዝ ችሏል።

ከሰሞኑ ስራ ፈቱ በረከት ስምኦን "የኤርትራ ተቃዋሚዎች አረብኛ ፓልቶክ" በተሰኘ የመወያያ መድረክ ላይ ቀርቦ ቃለመጠይቅ ሰጥቶ ነበር። የዚህ መጣጥፍ ቁምነገር በረከት ስምኦን ቃለመጣይቅ መስጠቱና አለመስጠቱ ላይ አይደለም። ቃለመጠይቅ መስጠትና አለመስጠት የራሱ ጉዳይ ነዉ። ሆኖም ቃለመጠይቁ አገርን ያክል ትልቅ ነገር የሚበክል መርዝ ስለነበረበት ማርከሻ ይሆነዋል በሚል የዚህን እብሪተኛ ሰዉ ቃለመጠይቅ በዚህ ጽሁፍ ለመዳሰስ ተገድደናል።

ጉዳዩ እንደዚህ ነዉ - በቅርቡ በረከት ስምኦን "አረቢክ" የሚባል ፓልቶክ መድረክ ላይ ቀርቦ ቃለመጠይቅ ሰጥቶ ነበር። ቃለመጠይቁ የኢትዮጵያ ጉዳይ እጅግ የሚያሳሳብቻዉን እትዮጵያዉያን ቀርቶ በኢትዮጵያና በህዝቦቿ ላይ ታሪካዊ ደባ የፈጸሙትን የህወሀት አባላትን ጭምር አስቆጥቷል። በረከት ስምኦን በዕለቱ ከተናገራቸዉ ብዙ የክህደትና የጥላቻ ንግግሮች ዉስጥ አንደኛዉ "አንድነትና አንድ አገር የሻዕቢያ መዝሙር ነዉ" የሚል ሲሆን ሌላኛዉ ደግሞ "ኢትዮጵያ ዉስጥ መገንጠል ለሚፈልጉ ግዜዉ ሲደርስ መገንጠል መብታቸዉ ነዉ" የሚል ነበር።

ለመሆኑ በረከት ስምኦን "አንድነትና አንድ አገር" የሻዕቢያ መዝሙር ነዉ ሲል ምን ማለቱ ነዉ? በረከትና የደደቢት ጓደኞቹ ኢትዮጵያን የሚመለከቷት እንደ አንድ ሉዓላዊ አገር ነዉ ወይስ ኢትዮጵያ እነሱ ሲፈልጉ አንድ የምትሆን እነሱ ካልፈለጉ ደግሞ ተገነጣጥላ ብዙ የምትሆን አገር ናት። በረከትና ወያኔ አዲስ አበባ ሲገቡ ኢትዮጵያ ስንት ነበረች ዛሬስ ስንት ናት? መቼም ወያኔና በረከት ስምኦን ሺ ግዜ ቢነገራቸዉ የማይገባቸዉ ጭራሽ ባይነገራቸዉም ቀረብን የማይሉ ግዑዝ ዕቃዎች ሆነዉ ነዉ እንጂ ከአራቱም ማዕዘን ስንቁን ተሸክሞ በእግሩ አድዋ ድረስ የተመመዉ የኢትዮጵያ ህዝብ መንገድ ላይ የዘመረዉ ብቸኛ መዝሙር "አገሬ ኢትዮጵያ" የሚል መዝሙር ነበር። በረከትና ጓደኞቹ የኢትዮጵያ ህዝብ አንድነትና የኢትዮጵያ አንደ አገር ላይጥማቸዉ ይችላል፤ ቁጥሩ ከ90 ሚሊዮን ባላይ አንደሆነ የሚገመተዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ግን ለአገሩ አንድነትና ሉዓላዊነት ህይወቱን ለመስጠት የማይሳሳ ህዝብ ነዉ። እዉነትም ሟርተኛዉ በረከት እንደተናገረዉ "አንድነትና አንድ አገር" የሻዕቢያ መዝሙር ከሆነ የእኛ የኢትዮጵያዉያን መዝሙርስ ምን ይሆን? ወይስ በረከት የሱን መዝሙር እኛም እንድንዘምርለት ይፈልጋል!

ሌላዉ በረከት ስምኦን የተናገረዉና አንድነቱን የሚወድደዉን የኢትዮጵያን ህዝብ እጅግ ያበሳጨዉ ንግግር "ኢትዮጵያ ዉስጥ መገንጠል ለሚፈልጉ ሁሉ ግዜዉ ሲደርስ መገንጠል መብታቸዉ ነዉ" ብሎ የተናገረዉ ንግገር ነዉ። በሚሎዮን የሚቆጠሩ ዜጎች በየዘመኑ በከፈሉት የህይወት መስዋዕትነት ተጠብቆ የኖረዉን የኢትዮጵያን አንድነት በረከት ስምኦን እንደቀላል ነገር በግዜ ገድቦ ነበር ያስቀመጠዉ። ሁላችንም በግልጽ እንደምናዉቀዉ ይህ የበረከት ስምኦን ንግግር አዲስ አይደለም፤ ወያኔ ከጫካ ጀምሮ የተከተለዉ ፀረ ኢትዮጵያ እስትራቴጂ ነዉ። የወያኔዎች አላማ አቅሙ እስከፈቀደ ድረስ ተቃዋሚ ሀይሎችን አጥፍቶ ኢትዮጵያን እየዘረፉ መኖር ነዉ። ተቃዋሚዎች አይለዉ የወያኔ ስልጣን አደጋ ላይ ይወድቃል ብለዉ ከሰጉ ደግሞ እነሱ ትግራይን ተቆጣጥረዉ ሌላዉን የኢትዮጵያ ክፍል በታትነዉ መሄድ ነዉ። በረከት ስምኦን በሰጠዉ ቃለ መጠይቅ ላይ "ግዜዉ ሲደርስ" መገነጣጠል ይቻላል ያለዉም ይህንኑ ጫካ ዉስጥ እያሉ ተዋዉለዉ የመጡትን ኢትዮጵያን የማጥፋት ዉል ለመጠቆም ነዉ።

መለስ ዜናዊ በህይወት በነበረበት ወቅት ደጋግሞ አንደተናገረዉም ይሁን ዛሬ በረከት በየፓልቶኩ መድረክ እንደሚለፈልፈዉ እቺ ኢትዮጵያ ተብላና ዘመናትን አቋርጣ እኛጋ የደረሰችዉ የጀግኖች አገር "ግዜዉ ሲደርስ" በትንሹ ከሁለት እስከ ዘጠኝ ትናንሽ አገሮች ልትቆራረስ ትችላለች። ባጠቃላይ እንደነበረከት አባባል ኢትዮጵያ ብሔር ብሄረሰበቿ ደስ ሲላቸዉ የሚተክሏት ሲከፋቸዉ ደግሞ ነቃቅለዉ የሚያፈርሷት የእድር ድንኳን ናት። እንግድህ እነዚህ ናቸዉ የኢትዮጵያን ህዝብ አስተባብረዉ አባይ ወንዝ ላይ ግድብ የሚሰሩት . . . ነገ የማን መሆኑ እንኳን የማይታወቅ ግድብ! እነዚህ የነገይቱ ታላቅ ኢትዮጵያ ራዕይ የሌላቸዉ ከሀዲዎች ናቸዉ በኢትዮጵያ ስም በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ የሚበደሩትና በኢትዮጵያ ሰም አለም አቀፍ ዉሎችን የሚፈራረሙት! አቤት እግዚኦ! አቤት ኢትዮጵያ. . . . እቺ ናት የመለስ ራዕይ!

ይህንን "መገንጠል" የሚሉትን በወያኔ ህግ መንግስት ዉስጥ የተቀመጠዉንና እነ በረከት ስምኦን ዛሬም ድረስ የሚያጠነጥኑትን የባለጌ መዝሙር አፋችንን ከፍተን የምንሰማ ከሆነ መናገሻ ከተማችን አዲስ አበባ፤ዉብ ከተሞቻችን አዋሳ፤ ባህርዳር፤ ጂማና ናዝሬት፡ ታሪካዊ ከተሞቻችን አክሱም፤ ላሊበላ፤ ጎንደርና ደብረበርሀን የጀግኖቻችን አጽም ያረፉባቸዉ ቦታዎች እነ መቅደላ፤ መተማ፤አድዋ፤ማይጮዉና ወልወል እንደዚሁም የቡና መሬቶቻችን ዲላ፤ግምቢና አጋሮ እነ በረከት "ግዜዉ ሲደርስ" ያሉት ግዜ ሲደርስ ኢትዮጵያ ከሚባል ታሪካዊ ስም ጋር የነበራቸዉና አሁንም ያላቸዉ የደም፤ የመስዋዕትነትና የአብሮ መኖር ወንድማማችነት ግንኙነት እንዳልነበረ ሊሆን ነዉ ወይም ዛሬ አንድ የሆነዉ የኢትዮጵያ ህዝብ የነበረከት ግዜ ሲደርስ "እኛና እነሱ" ልባባል ነዉ።

ዉድ ኢትዮጵያዉያን ይህ እንደ ሰማይ የገዘፈ ጥፋት "ሰዉረነ ከመአቱ ....አድነነ ከጥፋቱ" ብለን አማትበን የምናልፈዉ ተራ ጥፋት አይደለም። ደግሞም ይህ ግዙፍ ጥፋት የተዶለተዉ በእኛ ዛሬ በህይወት ባለነዉ ኢትዮጵያዉያን ላይ ብቻ አይደለም። ይህ ታሪካዊ ጥፋት እቺን አገር አደራ ጥለዉልን ባለፉት በአባቶቻችን ላይ፤ በእኛ ላይና በመጪዉ ትዉልድ ላይ ሁሉ የተዶለተ ትዉልድን ወደኋላና ወደፊት ያጣቀሰ ጥፋት ነዉ። ሆኖም አባቶቻችን ሐላፊነታቸዉን ተወጥተዉ ስላለፉ መጪዉ ትዉልድ ደግሞ ገና ስላልተወለደ ይህንን ጥፋት ማስቆም ብቻ ሳይሆን የጥፋቱን መሐንዲሶች መደምሰስ የዚህ ትዉልድ ሐላፊነት ነዉ።

በረከትና ጓደኞቹ የአገራችንን ጉደይ "ግዜዉ ሲደርስ" ብለዉ ነግረዉናል። ወገን ግዜዉ ደርሷል. . . ግዜዉ ዛሬ ነዉ! እቺን ከአባቶቻችን በአደራ የተረከብናትን አገር እኛም ለልጆቻችን በአደራ ለማስረከብ የተዘጋጀን ኢትዮጵያዉያን ሁሉ "ነፃነት ወይም ሞት" ብለን የምንነሳበት ቀን ዛሬ ነዉ። እኛ ሞተን ኢትዮጵያን በህይወት ማቆየት ከተሳነን ታሪክና ትዉልድ የሚያስታዉሱን "አደራዉን የበላ ትዉልድ" እያሉ ነዉ። ለአገሩ መሞትን ፈርቶ ይህንን ከሞት በላይ የከፋ ዘለአለማዊ ስም መቀበል የሚፈልግ ኢትዮጵያዊ ደግሞ በታሪካችን አልነበረም፤ ዛሬም የለም ለወደፊትም አይኖርም። እንግዲህ የእናት ኢትዮጵያን ትንሳኤ እዉን ለማድረግ ትግሉን የተያያዝነዉ ሁሉ ሞት በሌለበት ትንሳኤ የለምና ለሞትና ለመስዋዕትነት የምንዘጋጅበት ግዜዉ አሁን ነዉ።

## ኢትዮጵያ ዉስጥ የኑሮ ውድነት ሕዝብን. . . (ከገጽ 4 የዞረ)

ዜጎችና ጧሪ ቀባሪ የሌላቸው ሽማግሌዎች፤ ባልቴቶች ህፃናትና በአነስተኛ ገቢ የሚተዳደሩ ሰዎች ናቸዉ። ዛሬ የቤት ኪራዩ ሰማይ ነው፤ አንድ ኪሎ ሽሮ 30 ብር፣ ኪሎ ምሥር 30 ብር፤ኪሎ ሥጋ 120 ብር ደርሷል" ተራ ሬስቶራንቶች ዉስጥ የአንድ ምሣ ዋጋ ከ25 ብር በላይ ነው ብሏል። በእርግጥም ዛሬ ኢትዮጵያ ዉስጥ ህዝቡ ምን በልቶ እንደሚያድር የሚያዉቀዉ ፈጠሪ ብቻ ነዉ፤ ኢትዮጵያ ህዝብም ቢሆን ከመንግስት በኩል ክፋትና በደል እንጂ ሌላ ምንም እንደማይገኝ አዉቆ ከአሁን በኋላ መፍትሄ ይገኛል ብሎ የሚጠብቀዉ የወያኔን ስርአት ለመደምሰስ ከሚታገሉ ተቃዋሚ ሀይሎች ብቻ አንደሆነ ብዙዎች በግልጽ በመናገር ላይ ናቸዉ።

## ኢትዮጵያ የመንግስታቱ ጉባኤ የሰብአዊ መብቶች ጉባኤ አባል ሆና መመረጧ ብዙዎቹን ኣሳቀ

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብአዊ መብቶች ጉባኤ ባለፈዉ ሰኞ ህዳር 3 ቀን 2005 ዓም ባካሄደዉ ጉባኤ ኢትዮጵያን ጨምሮ ሌሎች ስድስት በሰዉ ልጅ መብት ረጋጭነታቸዉ የሚታሙ አገሮችን የጉባኤዉ አባል አድርጎ መምረጡ አያሌ ኢትዮጵያዉያንና የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶችን ማስቆጣቱ ታወቀ። ኢትዮጵያን የመሰለ የአለማችን ቁጥር አንድ የሰብዓዊ መብቶች ረጋጭ የሆነ አገር በአለማችን በተለያዩ አገሮች ዉስጥ የሚካሄደዉን የመብት ረገጣ ለሚከታተለዉ ጉባኤ አባል አድርጎ መምረጥ "መልከ ጥፉን በስም ይደግፉ" የሚለዉን ቆየት ያለ ተረትና ምሳሌ በተግባር ለማረጋጥ ካልሆነ በቀር ሌላ ምንም ፋይዳ የለዉም ሲሉ በአለም ዙሪያ የሚገኙ ኢትዮጵያዉያን የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች የኢትዮጵያን የስብዓዊ መብቶች ጉባኤ አባል ሆኖ መመረጥ አጥላልተዋል። በተለይ አንድ ኒዮርክ ዉስጥ የሚገኙ ኢትዮጵያዊ የህግ ምሁር የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብአዊ መብቶች ጉባኤ ግዙፍ ድርሳኖችን ከማዘጋጀት ዉጭ ምንም አይነት ተጨባጭ ስራ መስራት የማይችለዉ በየግዜዉ ኢትዮጵያን የመሳሰሉ የለየላቸዉ የሰብዓዊ መብት ረጋጮችን የጉባኤዉ አባል አድገርጎ ስለሚመርጥ ነዉ ብለዋል።

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብአዊ መብት ጉባኤ ከኢትዮጵያ ሌላ አይቮሪኮስትን፣ ጋቦንን፣ ካዛኪስታንን፣ ፓኪስታንን፣ ዩናይትድ አረብ ኤምሬትንና ቪንዙዌላን የመሳሰሉ ከፍተኛ የሰብአዊ መብት አያያዝ ችግር ያለባቸውን አገሮች የጉባኤዉ አባል አድርጎ መርጧል። ኢትዮጵያ በሰብአዊ መብቶች አያያዟ በተደጋጋሚ እንደምትተች የሚታወቅ ሲሆን ይህንኑ በሚመለከት የተመድ የሰብዓዊ መብቶች ተቋም ዳይሬክተር የሆኑት ፊሊፒ ቦሎፒዮን የኢትዮጵያን አስከፊ ሰብአዊ መብቶች ጥሰት አጉልተው በማውጣት ተችተዋል። የኢትዮጵያ መንግስት ይህን እድል በመጠቀም ሀሳብን በነጻነት የመግለጽና የመደረጃት መብቶችን እንዲያከበድር፣ የጸጥታ ሀይሎች በሚፈጽሙት የሰብአዊ መብት ጥሰት በህግ ተጠያቂ የሚሆኑበት አሰራር እንዲጀምርና፣ እንዲሁም አገሪቱ አሁን አባል ሆና ለተመረጠችበት የሰብአዊ መብቶች ጉባኤ ቀና ትብብር እንዲያሳይ ዋና ዳይሬክተሩ የኢትዮጵያን መንግስት ተማጽነዋል።

### የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ንቅናቄ አሁን ባለበት መልኩ ከቀጠለ ለአፍሪካ ቀንድ አሳሳቢ ነዉ ተባለ

ምንም አይነት እልባት ሳያገኝ ከአንድ አመት በላይ የዘለቀዉ የኢትዮጵያ እስልምና እምነት ተከታዮች የመብትና የነፃነት ትግል የወያኔ አገዛዝ የእስልምና ምክር ቤቱንና የእምነቱን ስርአት ለመቆጣጠር ከሚያደረገው አሳፋሪ ጥረት ዉጭ የመብት ጥያቄዉን ለመመለስ የሚያደርገዉ ምንም አይነት ጥረት ባለመኖሩ እንቅስቃሴዉ ከሀገሪቱ አልፎ የአፍሪካን ቀንድ የእሳት ረመጥ ዉስጥ ሊከትት የሚችል መሆኑ ተገለጠ:: ወያኔ የሙስሊሙን ህብረተሰብ የአመራር ማእከልና የማህረሰቡን ተቃውሞ በሀይል ለመቆጣጠር የሚያደርገው ጥረት የሙስሙን ማህበረሰብ ብቻ ሳይሆን የሁሉምን አገሪቱ ዜጎች ቁጣና ተቃዉሞ እየቀሰቀሰ መሆኑን ከኢትዮጵያ የሚደርሱን የተለያዩ ዜናዎች ያስረዳሉ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ አለም አቀፉ የአሜሪካ የሐይማኖት ነጻነት ኮሚሺን ሰሞኑን ባሰራጨዉ ዜና የኢትዮጵያ መንግስት በሰላማዊ መንገድ የማምለክ መብታቸዉ እንዲከበር የጠየቁ ኢትዮጵያዉያን የእስልምና እምነት ተከታዮችን በሽብርተኝነት እየፈረጀ ማሰሩ ህግ ወጥ ተግባር ነዉ ሲል ድርጊቱን አጥብቆ ኮነነ። የኮምሽኑ ሊቀመንበር ወይዘሮ ካትሪና ላንቶስ የዩናይትድ ስቴት መንግስት በዚህ ጉዳይ ላይ ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር መነገጋር እንዳለበት ገልጸዉ የሀይማኖት ተከታዮችን በአሸባሪነት ስም ለማፈንና ለማሰር የሚደረገዉ ጥረት አክራሪነትንና አለመረጋጋትን ያባብሳል አንጂ መፍትሄ አይሆንም በማለት የወያኔን የሀይል እርምጃ ነቅፈዋል።

### ወያኔ አገዛዝ የቤት ልማት ፕሮግራሙን ከምርጫ ጋር የሚያስተሳስር ንድፍ እየነደፈ መሆኑ ተጋለጠ

በቁጠባ ላይ የተመሰረተዉንና 40 በ60 በመባል የሚታወቀዉን የመኖሪያ ቤት ግንባታ የስራ እንቅስቃሴ በአዲስ አበባና በአካባቢዋ ከሚካሄደዉ ምርጫ ጋር ለማያያዝ ወያኔ እቅድ ነድፎ በመንቀሳቀስ ላይ መሆኑን አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙ የግንቦት ሰባት ምንጮች ለዝግጅት ክፍላችን በላኩት ዜና ገለጹ። ይህንን አዲስ አበባ ዉስጥ በከተማ ልማትና ኮንስትራክሺን ሚኒስቴር አመራር ሰጪነት ለመጀመር የታቀደውን ፕሮጀክት ከምርጫው ጋር ለማያያዝ የተፈለገው ሕዝቡ የወያኔ/ኢህአዴግ አገዛዝ ለልማት የሚያደርገውን ጥረት ተረድቶ ልማቱ እንዲቀጥል ከፈለገ ከወያኔ ሌላ አማራጭ እንደሌለ ከወዲሁ ለመስገንዘብ አንደሆነ ታዉቋል። በዚህም መሠረት ለ40 በ60 ቤቶች ፕሮግራም የሚደረገው ምዝገባ ለምርጫዉ ከሚደረገዉ ምዝገባ ጋራ በአንድ ላይ አንዲጀመር በማድረግ ወያኔ ይህንን እኩይ እቅዱን የሚያስፈጽሙ ካድሬዎቹን ከአሁኑ በየቦታዉ መላክ ጀምሯል።

በሌላ በኩል ደግሞ ምዝገባዉ የሚካሄደዉ የወያኔ ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ቢሮ በሚቆጣጠረዉ የኤሌክትሮኒክስ ዘዴ በመሆኑ ህዝቡ ለቤት ምዝገባ የሚሰጣቸዉን መረጃዎች ገዥው ፓርቲ በቀላሉ ለስለላ ተግባር ይጠቀምበታል የሚለዉ ስጋት እየተጠናከረ መጥቷል። የወያኔ ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ቢሮ ከፍተኛ በጀት ከሚመደብላቸዉ የመንግሰት መስሪያ ቤቶች አንዱ ሲሆን በ2004 ዓም 74 ሚሊዮን ብር የነበረዉ የስለላ ቢሮዉ በጀት በ2005 ዓም ወደ 128 ሚሊዮን ብር ከፍ ብሏል። የዚህ መ/ቤት ብቸኛ ስራ የኢትዮጵያን ህዝብ በመረጃ ምንጭነት የሚያገለገሉትን መገናኛ ብዙሃንንና ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎችን ማፈን መሆኑ ይታወቃል::

### የመለስ ፎቶ አገር አስለቀቀ

ከኢትዮጵያ የሚደርሱን መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በየከተማዉ የሚገኙት መንገዶች፤አደባባዮች፤አጥሮችና ህንፃዎች በመለስ ዜናዊ ፎቶ በመጥለቅለቅ ላይ መሆናቸዉ ታወቀ። አዲስ አበባንና ድሬደዋን ጨምሮ በዘጠኙም ክልሎች የሚገኙ ዘጋቢዎቻችን በፎቶግራፍ አስደግፈዉ በላኩልን መረጃ መሠረት የመለስ ዜናዊ ፎቶ በትላልቅና በትናንሽ ቅርጾች በፖስተሮች፤ በቢልቦርዶችና በትናኝሽ ወረቀቶች ተለጥፎ በሁሉም ክልሎች በተለይም በትግራይ ከማጀት እስከ አደባባይ ተሰቅሎ እንደሚገኝ ለማወቅ ተችሏል። ይህ መለስ ዜናዊን ከሰዉነት ዉጭ በአማልክት ደረጃ ለማስቀመጥ የሚደረገዉ ትልቅ ዘመቻ የተቀነባባረዉ በህወሀት ካድሬዎች ሲሆን በየክልሉ የሚገኙት ምስለኔዎችና ተለጣፊ ድርጅቶችም በዚህ አሳፋሪ ስራ ላይ ተሰማርተዋል። አንድ ዝግጅትክፍላችን ድረስ ስልክ ደዉለዉ ያናገሩን የአዲስ አበባ ነዋሪ አንድ የከተማዉ ነዋሪ ከቤቱ ወጥቶ እስከሚገባ ድረስ በትንሹ ከአስር ግዜ በላይ የመለስን ፎቶ እንደሚያይ ተናግረዉ የወያኔ ካድሬዎች በዚህ ህዝብንም ሆነ አገርን በማይጠቅም ስራ ገንዘብና ግዜ ከሚያጠፉ ፊታቸዉን ወደ ልማት ስራዎች ቢያዞሩ አገራችን በፍጥነት ማደግ ትችል ነበር ብለዋል።

የአዲስ አበባ ዉስጥ ከመስቀል አደባባይና አካባቢው ሌሎች ማስታወቂያዎች ተነስተው የሰዉ አይን በቀጥታ በሚያርፋባቸዉ ቦታዎች ላይ ሁሉ የመለስ ዜናዊ ፎቶ በመለጠፍ ላይ ነዉ። ከዚህ በተጨማሪ በመስሪያ ቤቶች ዉስጥ በእያንዳንዱ የስራ ሐላፊ ቢሮና በመተላለፊያ ኮሪደሮች፣ በየመኪናው፣ በየመዝናኛው ቦታና በየሆቴሉ የዚህ ህዝብ ያሰቃየ ሰዉ ፎቶ ተለጥፏል። አንድ በቅርቡ ከአዉሮፓ ዘመድ ጥየቃ አዲስ አበባ ጎራ ብለዉ የተመለሱ የህግ ምሁር ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት ቃለመጠይቅ ከዚህ በፊት ሰሜን ኮሪያ ዉስጥ ለመሪዎች የሚደረገዉ ቅጥ ያጣ ግርግር ይገርመኝ ነበር በቅርቡ አዲስ አበባ ዉስጥ ያየሁትን አይነት መንግሥታዊ ማይምነትና አጭበርባሪነት ግን በታሪክም አላነበብኩም፤ በተዘዋወርኩባቸው በርካታ የዓለም ሀገራትም አላየሁም ብለዋል።

### ኢትዮጵያ ዉስጥ የኑሮ ውድነት ሕዝብን አስለቀሰ

በኢትዮጵያ ዉስጥ በየሰአቱ የሚያድገዉ የአገልግሎትና የዕቃዎች ዋጋ የፈጠረዉ የኑሮ ዉድነት የአብዛኛዉን ኢትዮጵያዊ እስትንፋስ ወደ ማቆም ደረጃ መድረሱን አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙ ምጮቻችን አገዛዙ በቅርቡ ያወጣቸዉን የዋጋ ዝርዝር መለኪያ መረጃዎች ጠቅሰዉ በላኩልን ዜና ገለጹ። ከሰራተኛ ደሞዝ አለመስተካከል፤ከብር ዋጋ መዋዠቅና ከመነግስት ከአቅም በላይ መበደር ጋር በተያያዘ መንገድ እንደ መንፈቅ ልጅ በየቀኑ የሚያድገዉ የዕቃዎች ዋጋ ህዝቡን በተለይ የከተማ ነዋሪዉን ክፉኛ እንደጎዳዉ ለማወቅ ተችሏል። "እህል ከቀመስኩ ሦስተኛ ቀኔ ነዉ" ከሚለዉ ከተሜ "ረሀቡ ፈጀን" እስከሚለዉ ባላገር ድረስ ሽማቹንና አምራቹን ህብረተሰብ የናገረዉ ዘጋቢያችን ከዚህ ቀደም አምስትና አስር ብር ያለዉ ሰዉ ለሌሎች ይተርፍ እንደነበር አስታዉሶ በአሁኑ ወቅት ግን የብር የመግዛት አቅም ቁልቁል በመዉረዱ ሀምሳ ብር ያለዉ ሰዉ እራቱን ከገዛ ለቁርስ እንደማይተርፈዉ ተናግሯል።

በሌላ በኩል ደግሞ አንድ በቅርቡ ከደቡብ ዩኒቨርሲቲ የተመረቀ ወጣት ለዘጋቢያችን እንደተናገረዉ "እኔ ብዙም ግድ የለኝም ባጣ ባጣ ለሆዴ አላጣም" እኔን የሚያሳዝኑኝ ምንም አይነት ገቢ የሌላቸው . . . (ከገጽ 3 ዞሯል)

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz
<u>አጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org